ቁጥር 3 ጥቅምት 2015 3ኛ ዕትም በነፃ የሚታደል




ቁጥር 3 ጥቅምት 2015 3ኛ ዕትም በአዲስ አበባ ኮሙኒኬሽን ቢሮ

## የምዕራፍ ሁለት የወዳጅነት ፓርክ





የአዲስ አበባ ከተማን ገፅታ ከቀየሩ ፕሮጀቶች አንዱ የወዳጅነት ፓርክ ፕሮጀክት አካል የሆነው ምእራፍ ሁለት ግንባታው ተጠናቆ ባለፈው ሳምንት በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ተከፍቶ ለጐብኚዎች ክፍት ተደርጓል፡፡

የምዕራፍ ሁለት የወዳጅነት ፓርክ በ11 ሺ ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን በውስጡ የህፃናት መጫወቻ ስፍራ፣ የወጣቶች የስፖርት ስፍራ፣ የሰርግ አፀድና ሌሎች መዝናኛዎችን የያዘ ለጐብኚዎች ምቹ የሆነ ቦታ ነው። በርካታ የከተማዋ ነዋሪዎች ልጆቻቸውን ይዘው፣ከወዳጅ ዘመዶቻቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ጉብኝት እያደረጉ ነው።

ህጻናት እየቦረቁ ነው፤ ወላጆች በልጆቻቸው ቡረቃ ተደስተዋል፤ ግቢውን በሞሉት ጎብኝዎች ፊት የሚታየው ደስታ ለተመልካች ይጋባል። ባሳለፍነው ሳምንት ተመርቆ በተከፈተውና ለአንድ ሳምንት ለህዝብ ክፍት ሆኖ በቆየው የወዳጅነት ፓርክ ምእራፍ ሁለት ግቢ ውስጥ የሚታየው ትዕይንት ቀልብን ይስባል።

# ምዕራፍ ሁለት ወዳጅነት ፓርክ 50 ጥንዶች በአንድነት ጋብቻቸውን ፈፀሙ



በአዲሱ ምዕራፍ ሁለት የወዳጅነት ፓርክ 50 የሚሆኑ ጥንዶችን የሠርግ ሥነ ስርዓት በማስተናገድ ጥቅምት 20 ለበርካታ ሙሽሮች የሰርግ ጥያቄ መልስ በመስጠት ለአገልግሎት ክፍት ሆኗል፡፡የፓርኩን መከፈት ምክንያት በማድረግ በተዘጋጀ ስነ ስረአት ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ እንደተናገሩት "ጋብቻ የሀገር መሠረት ከሆኑት ተቋማት አንዱ የሆነው ቤተሰብ የሚመሠረትበት ነው።" ብለዋል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው " የተለያዩ ሀገራዊና አህጉራዊ የሆኑ ኩነቶችን ለማዘጋጀት የምትፈልጉ የግልና መንግስታዊ ተቋማት በዚህ ስፍራ ማከናወን የምትችሉ መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ" ብለዋል።ፓርኩ ለሠርግ ሥነ ስርዓት የሚሆን “የሠርግ አጸድ” የተባለ ሥፍራን አካቶ በተገነባው በዚህ ፓርክ በተካሔደው የሠርግ ሥነ ስርዓት ላይ የተሞሸሩ ጥንዶች፣ በዚህ መልኩ የሠርግ ድግስ ማድረግ ከወጪ እንዲሁም ትውውቅ ከመፍጠር አንጻር አስተዋጽኦው የጎላ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ከቲባ አዳነች አቤቤ

## የታላቁ ቤተ መንግስት ቅርስና መኪና ማቆሚያ ፕሮጀክት

የታላቁ ቤተ መንግስት ቅርስና መኪና ማቆሚያ ፕሮጀክት ሁለገብ አገልግሎት መስጠት እንዲያስችል ተደርጎ እየተገነባ ነው፡፡

የፕሮጀክክት ግንባታው በውስጡ አራት ደረጃዎች (4 Basement) ያሉት የመኪና ማቆሚያን፣ የተለያዩ ሱቆች፣ የካፍቴሪያ አገልግሎት፣ አምፊ ቲያትር፣ የኢንተርኔት አገልግሎት መስጫ፣ የስራ ቢሮዎችና ሌሎች ሁለገብ አገልግሎቶችን መስጠት እንዲያስችል ምቹና ውብ ተደርጎ የታነፀ ሁለገብ አገልግሎት መስጫ ህንፃ ነው ፡፡ ከከፍተኛ አመራሩ ጀምሮ በየደረጃው ባሉ የግንባታው ዘርፍ አካላት ልዩ ድጋፍና ክትትል እየተደረገለት በማጠቃለያ ምዕራፍ ላይ የሚገኘው የታላቁ ቤተ መንግስት ቅርስና መኪና ማቆሚያ ፕሮጀክት አሁን ላይ ለተቋሙና ለውጭ ተገልጋዮች የሚሆኑ ማረፊያ ወንበሮች፣ ጠረጴዛ፣ ቁሳቁስ ማስቀመጫ ቁም ሳጥኖች ፣ መመገቢያ ጠረጴዛዎች እና መሰል መገልገያ ቁሳቁሶችን የማስገባትና ተቋሙን የማደራጀት ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ።





ቁጥር 3 ጥቅምት 2015 3ኛ ዕትም በነፃ የሚታደል

# ከተማዋ በሁለት አለም አቀፍ አርዓያነት ያላቸው ሥራዎች ተሸላሚ ሆነች።





የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ብራዚል በተካሄደው የ "Milan Urban Food Policy Pact" ዓለማቀፍ ፎረም በተማሪዎች ምገባ ፕሮግራምና አርጀንቲና በተካሄደው በ C40 የከንቲባዎች ፎረም በካይ-ጋዝ እና በቆሻሻ አወጋገድ ከተማ አስተዳደሩ አርዓያ ሥራ በማከናወን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳድራ ተሸላሚ ሆነች።

ከተማዋ በትምህርት ቤቶች ከ628 ሺህ በላይ ተማሪዎችን ተጠቃሚ ያደረገ የምገባ ፕሮግራም' ተግባራዊ አድርጋለች። የተማሪዎች ምገባ ፕሮግራም ከዚህ ቀደም ተማሪዎች በረሃብ ይወድቁ ከነበረበት ዛሬ ተማሪዎች በተረጋጋ ሁኔታ የሚማሩበት፣ መጠነ ማቋረጥ የቀነሰበት፣ የውጤት መሻሻል የታየበት፣ ወላጆች ከብዙ ጭንቀት እፎይ ያሉበት ፕሮግራም በመሆኑ ተሸላሚ እንድትሆን አድርጓታል።

በተመሳሳይ ከተማዋ የበካይ ጋዝን በሚያስቀር የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ስርአት በመዘርጋት ባከናወነችው መልካም ስራ በC40 የከንቲባዎች ፎረም ታላቅ ውድድር አሸናፊ ሆናለች፡፡

አዲስ አበባ ከተማ እ.ኤ.አ ከጥቅምት 19 እስከ 20/2022 በአርጀንቲና ቦነስአይነስ በተካሄደው የ C40 የአለም ከንቲባዎች ፎረም ላይ የአየር ንብረትን የሚከላከል ተስማሚና ተመልሶ የመጠቀም አሰራርን የተከተለ የቆሻሻ አወጋገድ ስርአት በመዘርጋት አርንጓዴና ጤናማ ከተማ በመገንባት ሂደትና ቆሻሻን ወደ ኮምፖስት በመቀየር የገቢ ማስገኛ ስራ በማዋል ጉልህ ድርሻ በማበርከት መልካም ተሞክሮ ተሸላሚ መሆን ችላለች፡፡

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሁለት አለም አቀፍ ሽልማቶች ላገኘችው ሽልማት አስተዋጽኦ ላበረከቱ ድርጅቶችና ግለሰቦች እውቅና ሰጠች



አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተማሪዎች ምገባና ደረቅ ቆሻሻን መልሶ በመጠቀም ዘርፍ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ድርጅቶችና ግለሰቦች እውቅና የመስጠት መርሃግብር በሚሌኒየም አዳራሽ አካሄዷል።

በመረሀ ግብሩ ከንቲባ አዳነች አበቤ እንደገለጹት ሽልማቱ ሊገኝ የቻለው መንግስት በነደፈው የስራ እቅድና በፈጻሚዎች ትጋት ነው። ይህን ሽልማት ላስገኙ የከተማ ውበት አምባሳደሮችና ለባለድርሻ አካላት ምስጋና አቅርበዋል።

በከተማ አስተዳደሩ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የከተማ ግብርናን በመተግበር በርካታ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን የተናገሩት ከንቲባዋ፣ ወቅታዊ ችግሮችን ከመፍታት አልፈን ብልጽግናንን ለማረጋገጥ ተግተን እንሰራለን ብለዋል።

በእውቅና መርሃግብሩ ላይ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ፣የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤ አቶ አገኘሁ ተሻገር፣ ሚኒስትሮች፣ የክፍለ ከተሞች ስራ አስፈጻሚዎች፣ አምባሳደሮች፣ አርቲስቶች፣ታዋቂ ግለሰቦች ተገኝተዋል።





ቁጥር 3 ጥቅምት 2015 3ኛ ዕትም በነፃ የሚታደል

# የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች በከተማ አስተዳደሩ እየተገነቡ ያሉ ሜጋ ፕሮጀክቶችን ጎበኙ





**በአዲስ አበባ ከተማ ኮሙኒኬሽን ቢሮ**

**የህዝብና ሚዲያ ግኑኙነትና ይዘት ዘርፍ የሚዘጋጅ ወርሃዊ ዜና መጽሔት**

**ስልክ**

**ኢሜል**

**ዌብ ሳይት**

የአዲስ አበባ ከተማ ኮሙኒኬሽን ቢሮ በከተማው እየተገነቡ የሚገኙ የተለያዩ ለሕዝብ የላቀ ጠቀሜታ ያላቸው ፕሮጀክቶችን አጠቃላይ የግንባታ ሂደት ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፤ ከተጠናቀቁ በኋላ ምን አይነት አገልግሎት እንደሚሰጡ ለማስገንዘብ በተመረጡ ሜጋ ፕሮጀክቶች የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ጉብኝት አድርገዋል።

በጉብኝቱ ወቅት የከተማ አስተዳደሩ ኮሙኒኬሽን ቢሮ ሃላፊ ወ/ሮ ጠይባ ሎና እንደገለጹት፣ የጉብኝት ዋና ዓላማ በከተማ አስተዳደሩ እየተገነቡ ያሉ ፕሮጀክቶች ህብረተሰቡ እንዲያውቃቸውና በባለቤትነት ስሜት እንዲይዝ ለማድረግ ነው ብለዋል። ከተጎበኙት ፕሮጀክቶች መካከል የታላቁ ቤተመንግስት ግራንድ የመኪና ማቆሚ፣ የልማት ተነሽ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ፣የትራፊክ ማኔጅመንት ማእከል፣ የህጻናትና ወጣቶች የቲያትር ህንጻ ፕሮጀክቶች ይገኙበታል።

የአዲስ አበባ የሜጋ ፕሮጀክቶች ጽህፈት ቤት ስራ አስኪያጅ ኢንጂነር ደቦ ቱንካ የግራንድ የመኪና ማቆሚያውን ባስጐበኙት ወቅት እንደገለጹት፣ የሜጋ ፕሮጀክቶች ጽህፈት ቤት ከተቋቋመ በሶስት አመት ውስጥ የመስቀል አደባባይ ፕሮጀክትን ጨምሮ ሶስት ፕሮጀክቶችን አጠናቆ አስመርቋል። የግራንድ መኪና ማቆሚያው አራተኛው ነው ብለዋል። ግራንድ የመኪና ማቆሚያ በቅርቡ ለምርቃት እንደሚበቃ ኃላፊዋ ገልፀዋል፡፡

# በከተማዋ መንግስት የሀገር ክብርና ሉዓላዊነት ለማስከበር እየወሰደ ያለውን እርምጃ በመደገፍና ሠልፍ ተካሂደ





"ለኢትዮጵያ እቆማለሁ ድምፄን አሰማለሁ" በሚል መሪ ቃል የምዕራባውያንን ያልተገባ ጣልቃ ገብነት የሚቃወም ህዝባዊ ሰልፍ በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ ተካሂዷል።በመርሀግብሩ ላይ የአዲስ አበባ ምክትል ከንቲባና የስራ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ሃላፊ አቶ ጃንጥራር አባይ ባስተላለፉት መልዕክት እኛ ኢትዮጵያውያን ልክ እንደ አባቶቻችን ሁሉ ኢትዮጵያ ከምትፈርስ እኛ ቀድመን እንሙት በማለት ኢትዮጵያ እንዳትፈርስ አድርገናታል ኢትዮጵያ በእናንተ በሁላቹም አያቶች ታፍራና ተከብራ የኖረች፤ የአፍሪካ የአይበገሬነት ተምሳሌት፤ የቅኝ ገዢዎችን ህልም ያመከነች ፤የአለም የጥቁር ህዝቦች የታሪክ ባለቤት ናት "ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የዚህ ታሪክ ባለቤቶች ደግሞ የመላው ኢትዮጵያ አባት፤ እናትና አያቶች መሆናቸውን ገልፀው አያቶቻችን ያቆዩልን ሀገር ዛሬም በቁርጥ ቀን ልጆቿ እየተጠበቀች ትገኛለች ነው ያሉት ምክትል ከንቲባው፡፡ወደፊትም ክብሯና ሞገሷ በአለም አደባባይ ይነግሳል ኢትዮጵያ በክብሩና በሀገሩ ሉአላዊነት ሲመጡበት የማይናወጥ ህዝብ ባለቤት መሆኗንም ጠቁመዋል፡፡

የዛሬ ሁለት ዓመት ሰራዊቱ ለዘመናት ሲጠብቀው በነበሩ የህወሀት እጆች ባልጠበቀው ሁኔታ አሳፋሪ ድርጊት እንደተፈጸመበት ያስታወሱት አቶ ጃንጥራር፤የአገር መከታ የሆነው መከላከያ ሰራዊታችን ሲደፈር ከፍተኛ የህዝብ ቁጣ በመፈጠሩ ሳንወድ በግድ ወደ ጦርነት ተገፍተን ገብተናል ብለዋል፡፡ጀግናው የመከላከያ ሰራዊትና መላው የጸጥታ አካል ላደረጉት ኢትዮጵያን የማዳን መስዋዕትነት ክብር ይገባቸዋል ሲሉም ምስጋና አቅርበዋል፡፡

## ጥቅምት 24ን "መቼም አንረሳውም"



ዕለተ ሰኞ ጥቅምት 23-2013 ዓ.ም ለጥቅምት 24 አጥቢያ የኢፌዲሪ መከላከያ ሰራዊት ሰሜን እዝ አባላት ሽበርተኛው ሕወሀት በክህደት ጥቃት መፈጸሙ ሁሌ የሚታወስና ፈፅሞ የማይዘነጋ እለት ነው። እለቱን ስናስብ ለአመታት ቤት ንብረታቸውን ትተው የአገርን ዳር ድንበር እና ሉአላዊነት ለማስከበር ሐሩር እና ቁሩ ሳይበግራቸው በቀበሮ ጉድጓድ የቆዩት እና የትግራይ ሕዝብ ችግር ችግሬ ብለው ካላቸው እያካፈሉ ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ ችግሮቹን ከማንም ቀድመው ሲጋፈጡ የኖሩ የሰሜን ዕዝ አባላት ላይ ታይቶም ተሰምቶም በማይታወቅ ጭካኔ በአሸባሪው ህዋሃት ባልጠበቁት እና ባላሰቡት ሰዓት የተካዱና አረመኔያዊ ጭፍጨፋ የተፈፀመባቸውን ጀግኖች ሰማዕቶቻችንን በልባችን ታትመዋልና መቼም አንረሳቸውም፡፡

# ለመዲናዋ ሰላምና ፀጥታ መረጋገጥ የሰላም ሰራዊት አባላት ሚና የጎላ ነው፡፡





በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ በአዲስ በተቋቋመው የህዝብ ዘርፍ የሰላም ሰራዊት አደረጃጀት ዙሪያ ላይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አካሂዷል።

የከተማችንን ሰላምና ጸጥታ ለማስፈን የሰላም ሰራዊት በደንብ እና በአዋጅ ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ከአስፈጻሚ አካላት ጋር የጋራ አድርጎ በቅንጅት መስራት እንደሚገባ በውይይቱ ላይ ተገልጿል።

በውይይት መድረኩ ላይ የአዲስ አበባ ሰላምና ጸጥታ ቢሮ የሃይማኖትና የሰላም እሴት ዳይሬክተር አቶ ተመስገን እጅጉ እንደገለጹት፡- ህብረተሰቡ በሰላምና ጸጥታ ስራዎች ላይ ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ በማድረግ ለከተማዋ ሰላምና ጸጥታ መረጋገጥ የሰላሙ ባለቤት መሆን እንዳለባቸው ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ ሊዲያ ግርማ የተደራጀው የሰላም ሰራዊት ከጸጥታ አካላት ጋር በመቀናጀት በከተማችን ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን እያደረገ ያለውን አስተዋጽኦ ቀጣይነት እንዲኖረው ሁሉም ባለድርሻ አካላት በመናበብና በመቀናጀት መስራት ይጠበቃል ብለዋል።

የመድረኩ ተሳታፊዎች በበኩላቸው የአደረጃጀቱ ደንብ በመናበብና በቅንጅት እንዲሁም ሁሉንም ባለድርሻ አካል ባለቤት ማድረግ፣ በመመሪያ በመደገፍ ተፈጻሚ እንዲሆን መደረጉ ይበልጥ ውጤታማ ያደርገዋል ብለዋል።

# የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አባላት የሳይንስ ሙዚየምን ጉብኝት

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ዋና አፈ ጉባኤ ወ/ሮ ቡዜና አልካድርን ጨምሮ የምክር ቤት አባላት እና የክፍለ ከተማው አፈ ጉባኤዎች በቅርቡ የተመረቀውን የአዲስ አበባ ሳይንስ ሙዚየምን ጎብኝተዋል።

የጉብኝቱ ተሳታፊዎች በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር እና በኢትዮ ቴሌኮም የተዘጋጁ ስራዎቻቸውን እና በአርቲፊሻል ኢንተለጀንት ቴክኖሎጂ የተሰማሩ የግል አልሚዎችን የፈጠራ ስራዎችን ጨምሮ ጎብኝተዋል።

በጉብኝቱ የተሳተፉት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አባላት በሳይንስ ሙዚየሙ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን፣ የጤና ችግር ለሚገጥማቸው ሰዎች ከቤት ውስጥ ሆኖ የተለያዩ በሽታዎችን መለየትና መታከም የሚያስችሉ፣ለአፈር ምርምርና የአየር ንብረትን ለማወቅ የሚያስችሉ የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ እና የፈጠራ ስራዎችን የጎበኙ ሲሆን በተሰራው ስራ መደሰታቸውን ተናግረዋል፡፡

የሳይንስ ሙዚየሙን በከተማዋ በሚገኙ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በስፋት እየተጎበኘ ነው።





## የከተማችንን ነዋሪዎች የቤት ጥያቄ ለመመለስ የመንግስት ጥረት ብቻውን የሚፈለገውን ውጤት ሊያመጣ አይችልም፡፡








የመዲናዋን ነዋሪዎች የቤት ጥያቄ ለመመለስ የመንግስት ጥረት ብቻውን የሚፈለገውን ውጤት ሊያመጣ እንደማይችል እና የግል ባለሃብቱ በተዘረጋው የቤት ልማት የተለያዩ ፕሮግራሞች ላይ በመሳተፍ ተደራራቢ የቤት ጥያቄዎችን ለማቃለል የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊያበረክት እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ ገለፁ፡፡ከንቲባ አዳነች በሳኩር ሪልስቴት የተገነቡ 116 ቤቶችን እንዲሁም በአልሳም ግሩፕ የተገነቡ 360 ቤቶች እና የንግድ ሱቆችን ጨምሮ ገንብቶ ያጠናቀቃቸውን ቤቶች ተገኝተው አስመርቀዋል፡፡

የተመረቁት ቤቶች ግንባታ በቦታ አጠቃቀም፣ በዘመናዊነት፣ በጥራት የከተማዋን ገፅታ በመቀየር፣ የአኗኗር ባህልን በማሻሻል፣በስራ እድል ፈጠራ የራሱ የሆነ ሚና ያለው እንደሆነም ከንቲባ አዳነች ጠቁመዋል፡፡

## የሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት እድሳቱ ተጠናቆ ተመረቀ



ከ30 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገበት የሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት እድሳቱን ጨርሶ ለአገልግሎት ክፍት ተደርጓል።

በ1927 ዓ.ም እንደተመሰረተ የሚነገርለትና በርካታ አንጋፋ ከያንያንን ያፈራው ሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት አሁናዊ ገፅታውን ይዞ እንዲሰራ የተደረገው በ1994 ዓ.ም ነበር።

ይህን ገፅታውን በጠበቀ መልኩ በ2013 ዓ.ም የተጀመረው የቴአትር ቤቱ የእድሳት ስራ ተጠናቆ በዛሬው ዕለት ለአገልግሎት ክፍት መደረጉን ከአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ጽህፈት ቤት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

## በከተማዋ ከ239 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ በላይ የገፀ-ምድር እና የከርሰ-ምድር ውሃ የማልማት ሥራ እየተሰራ ነው



የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን 239.92 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ የገፀ-ምድር እና የከርሰ-ምድር ውሃን በማልማት ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ እየሰራ መሆኑን አሰታወቀ ::

የአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር ውሃ እና ፍሳሽ ባለጣልን በከተማችን ከህዝብ ቁጥር መጨመር ጋራ ተያይዞ የሚስተዋለውን የውሃ አቅርቦት እጥረት ለመቅረፍ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ እየሰራ መሆኑ ይታወቃል ::

በዘንድሮ በጀት ዓመት ከፕሮጀክቶች ግንባታ ጎን ለጎን ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን በጠበቀ መልኩ ከገጸ ምድር የውሃ መገኛዎች 74.46 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ እንዲሁም ከከርሰ ምድር የውሃ መገኛዎች 165.46 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ በማልማት ለነዋሪዎች ተደራሽ ለማድረግ ተግባራዊ እንቅስቃሴመጀመሩን ገልጧል ::

ባለፉት ሶስት ወራትም ከገጸ-ምድር እና ከከርሰ ምድር የውሃ መሰረተ ልማቶች 46.84 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ አምርቶ አሰራጭቷል፡፡

አዲስ የውሃ ጥያቄ ለሚያቀርቡ የተለያዩ አካባቢዎች ለአብነት ያክል በጋራ መኖሪያ ቤት ፕሮጀክቶች፣ ለሪል ስቴትና ለግሰብ መኖሪያ ግንባታዎች 52.036 ደንበኞች ብሎም ህጋዊ ሰነድ ለሚያቀርቡ ለ12,193 መደበኛ ደንበኞች በቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች አማካኝነት የውሃ ቅጥያ አገልግሎት ለመፈጸም የቅድመ ዝግጅት ስራዎቹን ማጠናቀቁን ባለስልጣኑ አክሎ አስታውቋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ የታገዱ አገልግሎቶችን ከመጀመሩ አስቀድሞ በሁሉም ህትመቶች ላይ የህትመት ለውጥ ማድረጉን የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ዮናስ አለማየሁ ገለፁ።

በከተማ አስተዳደሩ ተቋርጦ የነበረው የነዋሪነት መታወቂያ የእድሳት ከመጀመሩ በፊት ኤጀንሲው አስቀድሞ አገልግሎት ሲሰጥበት የነበረውን የልደት፣ የጋብቻ፣ የፍቺ፣ የጉዲፈቻ እና የሞት እንዲሁም የያላገባ እና የነዋሪነት መታወቂያ ካርዶችን ሰብስቦ ሙሉ ለሙሉ በማስወገድ የይዘት ለውጥ እና ተጨማሪ ምስጢራዊ ማሻሻያዎችን በማካተተ አዲስ ህትመት አሳትሞ መተካቱን የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ዮናስ አለማየሁ አሳውቀዋል።

በተለያየ ህገ-ወጥ መልኩ ከተቋሙ ወጥተው በሃሰተኛ ሰነድ አዘጋጆች እጅ ያሉ ማስረጃዎች ዋጋ እንዳይኖራቸው ለማድረግ በማሰብ እንዲሁም ጠንካራ የህትመት ስርጭት እና ቁጥጥር ስርዓት እንዲኖር ለማስቻል ጠንካራ አሰራር መዘርጋቱንም ሃላፊው ገልፀዋል።